21ኛ ዓመት ቁጥር 23
21th Year No.23

ባሕር ዳር ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም
Bahir Dar, January 02, 2017

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 46.46 ብር
Unit Price Birr 46.46

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር 242/2008 ዓ.ም**

**የተሻሻለዉ የአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞች ማቋቋሚያ ፤ ማደረጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ**

**Content**

**Proclamation No. 242/2016**

**The Issued Proclamation to Re-ammend the Revised Proclamation for the Establishment, Organization, and Determination of Powers and Duties of Urban Centers of the Amhara National Region**

## አዋጅ ቁጥር 242/2008 ዓ.ም

### የአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞችን ለማቋቋም፣ ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣውን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በክልሉ ውስጥ የሚገኙት የከተማ አስተዳደሮች፣ ማዘጋጃቤቶችና ታዳጊ ከተሞች ራሳቸውን ችለው መተዳደራቸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የሰው ሃይል ልማትና ስምሪታቸው ከክልሉ ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ፖሊሲዎችና ህግጋት ጋር ተሳስሮ የሚመራበትንና በዚሁ የማሻሻያ እርምጃ አማካኝነት ከተሞቹ ለነዋሪው ህዝብ የተሻለ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉበትን ህጋዊ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Proclamation No. 242/2016

### The Revised Proclamation for the Establishment, organization and Determination of powers and Duties of urban Centers of the Amhara National Region

WHERE AS, it is found necessary to create a legal condition that the urbans shall be able to render a better service to dwellers and the human resource development and their allocation to be managed, integrated with the regional civil service and human resource development policies and laws due to this amendment measure, without prejudice to city administrations, municipalities and emerging urban centers of the region;

በክልሉ ውስጥ በስራ ላይ የዋለውን ያልተማከለ የመንግስት አስተዳደር መርህ በሁሉም ከተሞች ዘንድ ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ እንደየ ከተሞቹ ደረጃ በተበታተነ መንገድ የሚሰራባቸውን የሰው ሃይል ቅጥር፣የደረጃ እድገት አሰጣጥ፣የስነ-ስርዓት እርምጃ አወሳሰድና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ወደ አንድ ወደ ተዋሃደ ማዕቀፍ ማጠቃለልና ለተጠያቂነት በሚያመች አደረጃጀት ጥላ ስርሆነው እንዲተገበሩ ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለዚሁ ያመች ዘንድ ከ12 ዓመታት ለዘለቀ ጊዜ ፀንቶ ሲሰራበት የቆየው የከተሞች አዋጅ የያዛቸውን አንዳንድ ድንጋጌዎች በጥናት ለይቶ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የአማራ ክልል ምክርቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ /49/ ንዑስአንቀጽ 3 /1/ ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

*1. **አጭር ርዕስ***

ይህ አዋጅ *"የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞች ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 242/2008 ዓ.ም"* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

*2. **ማሻሻያ***

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞች ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 91/1996 ዓ.ም /እንደ ተሻሻለ/ እንደገና እንደ ሚከተለው በዚህ አዋጅ ተሻሽሏል፦

ሀ/ የአዋጁ አንቀጽ /52/ ተሰርዞ ቀጥሎ በተመለከተው አዲስ አንቀጽ /52/ ተተክቷል፦

WHERE AS, it is found necessary that the recruitment, promotion, decipline measures taken and similar issues that have been implemented with disintegration as to the urban centers standard; to bne concluded into one frame work and to be implemented with organization suitable for accountability; that shall enable to be implemented the decentralized government. Administration principle which is in effect of the region to bring about to all urban centers;

WHERE AS, it is found necessary to revise some provisions of the urbans centers proclamation, identifying with sarrey, that it rendered servce for twelve 12 years sustainably,

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region in accordance with powers vested in it, under Article/49/ sub-article 3/1/ of the revised constitution of the National Regional State, hereby issued this proclamation.

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as "the Revised amhara National Region urban ceneters Establishment, Organization and powers and Duties Determination Proclamation Re-amendment proclamation No 242/2016."

***2. Amendment***

The revised amhara National Region urban centers Establishment, organization and Determination proclamation No. 31/2003 /as amended/ is amended as follows by this proclamation:

a/ Article /52/ of the proclamation is deleted and replaced with the following new Article /52/:

52. መሠረቱ

1. እያንዳንዱየከተማአስተዳደር፣ የማዘጋጃ ቤትም ሆነ ታዳጊ ከተማ በዚህ አዋጅ መሠረት የራሱን ምክርቤት የማቋቋምና የስራ አመራር አባላቱን የመሾም ስልጣን ይኖረዋል፤
2. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደ ተጠበቁ ሆነው እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር፣ የማዘጋጃ ቤትም ሆነ ታዳጊ ከተማ የራሱን ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የመቅጠር፣ የመመደብ፣ የማሳደግና እንደ አስፈላጊነቱ ከስራ ማሰናበትን ጨምሮ ጥፋት ፈጽመው ሲገኙ የስነ ስርዓት እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን ይኖረዋል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ስር በተደነገገው መሠረት የሚካሄደው የከተማ አገልግሎት ስራ አስኪያጆች ሹመት፣ የሠራተኞች ቅጥርና የደረጃ እድገት አሰጣጥ በእጩ ተሿሚው ወይም በተመልማዩ የግል ችሎታና የስራ ተስማሚነት ላይ ተመስርቶ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

ለ/ የአዋጁ አንቀጽ /53/ ሙሉ በሙሉ የተሰረዘ ሲሆን በዚሁ ነባር አንቀጽ መሠረዝ ምክንያት ቀደም ሲል በወጣው ሌላ ማሻሻያ አዋጅቁጥር 226/2007 ዓ.ም ምክንያት ከአንቀጽ /54/ እስከ አንቀጽ /74/ ሆነው የተስተካከሉት ድንጋጌዎች በዚህ ማሻሻያ መሰረት እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ /53/ እስከ አንቀጽ /73/ ሆነው የኁሊት ተሸጋሽገዋል፡፡

**52. Principle**

1. Each city administration, municipality as well as the emerging urban center shall have a power to establish its own council and appoint and management members in same;
2. Without prejudice to the provisions of this proclamation, each city administration, municipality, as well as, the emerging urban center shall have a power to recuti, assign , promote, as may be necessary including fire its own permanent and temporaray workers in accordance with the regional civil service laws, regulations and directivers and taking disciplinary measures where they are found commiting faults;
3. In accordance with the provision stipulated under sub article/2/ of this Article, the appointment of city service managers, the recruitment of employees and rendering promotion shall be implemented, based on private competence and work suitability of the candidate appointee or being selected person.

B/ Article /53/ of the proclamation is fully deleted, due to deletion of theis previous article and with other revised proclamation No of 226/2015, the corrected provisions from Articcle /54/ upto article /74/ aree arranged back from article/53/upto article /73/ respectively in accordance with this amenedment.

***3.የአዋጁ ማስፈፀሚያ ደንብ የተሻረ ስለመሆኑ፤***

የአዋጁን አንቀጽ /53/ መነሻ በማድረግ በክልሉ መስተዳድር ምክርቤት ወጥቶ እስካሁን ሲሰራበት የቆየው የከተማ አስተዳደሮችና የማዘጋጃ ቤቶች የሰው ሃይል አስተዳደር መወሰኛ ደንብ ቁጥር 25/1997 ዓ.ም በዚህ አዋጅ ተሸሯል።

4.በእንጥልጥል ላይ ስላሉና እልባት ስላላገኙ ጉዳዮች፤

ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት አግባብ ባላቸው የደንብ ቁጥር 25/1997 ዓ.ም ድንጋጌዎች መሰረት ለቀድሞው ክልል አቀፍ የከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች የሰው ሀይል አስተዳደር ቦርድ በይግባኝ ቀርበው መታየትና እልባት ማግኘት ሲኖርባቸው በእንጥልጥል የቆዩ ማናቸውም ጉዳዮች በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት ይህ ኣዋጅ ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ6(ስድስት) ወራት ጊዜ ውስጥ ለክልሉ ሲቢል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት አስተዳደር ፍርድቤት እየቀረቡ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኛሉ።

*3. __አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ__*

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ባህርዳር**

**ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም**

**ገዱ አንዳርጋቸው**

**የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚደንት**

**3.The Effect of Regulation of the proclamation is deleted**;

Incase of Article /53/ of the proclamation, the city administrations and municipality human resource administration determination regulationNo 25/2005 that has been in effect issued with the regional government council is deleted by this proclamation.

4. Pending issues that should have been seen with the relevant regulation No 25/2005 perovisions, presented with appeal to the previus regional city admibnistrations and municipality human resource administration board, shall get the decision, presented to the regional civil service and human resource development administration traibunal within 6/six/ months of this proclamation approval in accordance with provitions of this proclamation.

**3. __Effective Date__**

This proclamation shall come into forece as of the date of its official publication on the Zikre-Hig Gazzettee of the Regional State.

**Done at Bahir Dar,**

**This 2nd Day of January, 2017**

**Gedu Andargachew**

**President of the Amhara National Region**